## የፒስ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማኅበር
## የባለአክሲዮኖች 9ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ

1. ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት

ቦታ፡- ፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ ዋና መ/ቤት
ቀን፡- ህዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም.
ሠዓት፡- ከጠዋቱ 3፡00 - 4፡00 ሠዓት

2. የጉባኤው ጥሪ አደራረግ፣

ይህ የባለአክሲዮኖች 9ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ የንግድ ህግ አንቀጽ 370 መሠረት ሆኖ ከጉባዔው ዕለት 24 ቀናት አስቀድሞ በደብዳቤ ቁጥር PEACE/569/2022 በቀን ጥቅምት 19, 2015 ዓ.ም በተፃፈ እና በአድራሻ በተላከ ደብዳቤ እንዲሁም በስልክ ጥሪ ተደርጓል፡፡

3. ድምፅ ቆጣሪዎች፣ የማሕበሩ ፀሐፊና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት

3.1 ሰብሳቢ፣ ድምፅ ቆጣሪዎች እና የማህበሩ ፀሐፊ

በንግድ ህግ አንቀፅ 379 መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ጌታቸው ወርቁ የጉባኤው ሰብሳቢ ሲሆኑ፣ በንግድ ህግ አንቀጽ 380(1) መሠረት የጉባዔው ድምጽ ቆጣሪ የሚመረጠው ከተገኙት ባለአክሲዮች ከፍተኛ ድርሻ ባላቸው ባለአክሲዮኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት እንዲሆን የሚያዝ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ከተገኙት ባለአክሲዮኖች ከፍተኛ ድርሻ ባላቸው መካከል በተደረገ ስምምነት

1ኛ. ወ/ሮ ፍላጎት ለማ 2ኛ. አቶ አክሊሉ ታደሰ የጉባኤው ድምጽ ቆጣሪ እንዲሆኑ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

የማህበሩ ፀሐፊ እንዲሆኑ በዋና ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት በማህበሩ ቦርድ አፅዳቂነት የተመረጡት ወ/ሮ አዜብ በቀለ የማህበሩ ፀሐፊ ናቸው፡፡

| ተ/ቁ | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ | የጉባኤው ሰብሳቢ |
| 2 | ወ/ሮ ፍላጉት ለማ | ድምጽ ቆጣሪ |
| 3 | አቶ አክሊሉ ታደሰ | ድምጽ ቆጣሪ |
| 4 | ወ/ሮ አዜብ በቀለ | የማህበሩ ፀሐፊ |

3.2 በጉባኤው የተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣

| ተ/ቁ | ሥም | ተወካይ ከሆነ የተወካይ ሥም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | | የቦርድ ሰብሳቢ | |
| 2 | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | | የቦርድ አባል | |
| 3 | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻጊ | | የቦርድ አባል | |
| 4 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | | የቦርድ አባል | |
| 5 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | | የቦርድ አባል | |
| 6 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | ወ/ሮ ዓይናለም አሸብር | የቦርድ አባል | |

3.3 በጉባኤው ያልተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣

የለም

3.4 በጉባኤው የተገኘ ታዛቢዎች፣

| ተ/ቁ | ስም | የወከሉት ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ አመሐ ተካ | ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ |
| 2 | አቶ ሰለሞን ኃይለመለኮት | ቲ. ኤ. ዋይ የተፈቀደላቸው የሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች |

4. ምልዓተ ጉባኤው መሟላቱን ማረጋገጥ፣

የውይይቱ አጭር ቃል

ጠቅላላ የማኀበሩ አባላት ብዛት 16

ጠቅላላ የማኀበሩ የተፈረመ አክስዮን ብዛት 30,324

በስብሰባው የተገኙ አባላት ብዛት 13 የያዙት አክስዮን ብዛት 27,662 (91.22%)

በስብሰባው ያልተገኙ አባላት ብዛት 3 የያዙት አክስዮን ብዛት 2,662 (8.78%)

ለጉባኤው አስፈላጊ የሆነ የአክስዮን ብዛት 10,108 (33.33%)

በዚሁ መሠረት ከማሕበሩ ባለአክሲዮኖች ከ33.33% በላይ የሚወክሉ አባላት የተገኙ ስለሆነ በንግድ ህጉ አንቀፅ 402 መሠረት በጉባኤው አጀንዳ ላይ ተወያይተው ውሳኔ ማሳለፍ ሥልጣን ያላቸው መሆኑ በድምፅ ቆጣሪዎች ተረጋግጦ ጉባኤው ቀጥሏል። በጉባኤው ላይ የተገኙትንና ያልተገኙትን ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር እና የያዙትን አክስዮን መጠን የያዘ ሠንጠረዥ (Attendance Sheet) (ሠንጠረዥ-1) ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ሰነድ ጋር ተያይዟል።

## 5. የጉባዔው አጀንዳዎች

5.1 የጉባዔውን ረቂቅ አጀንዳ ማፅደቅ፤

5.2 የማህበሩን ካፒታል ለማሳደግ ተወያይቶ መወሰን

5.3 የጉባኤውን ቃለ-ጉባዔ ማጽደቅ፡፡

## 6. የጉባዔው ውይይት አጭር ቃልና ውሳኔ

### 6.1 አጀንዳ 5.1 የጉባዔውን ረቂቅ አጀንዳ ማፅደቅ፤

#### 6.1.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የጉባዔው ሰብሳቢ ጉባዔው ሊነጋገርበት ይገባል በማለት የቀረበውን ረቂቅ አጀንዳ በዝርዝር በማስረዳት ጉባዔው የአጀንዳውን አስፈላጊነት ተገንዝቦ እንዲያጸድቅ ተጠይቋል፡፡

#### 6.1.2 ውሣኔ፤

ጉባኤው የቀረበውን ረቂቅ አጀንዳ በሙሉ ድምጽ አፅድቋል፡፡

### 6.2 አጀንዳ 5.2 የማህበሩን ካፒታል ለማሳደግ ተወያይቶ መወሰን

#### 6.2.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የማህበሩ ካፒታል ወደ ብር 30,324,000 (ሰላሳ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ አራት ሺህ ብር) እንዲያድግ በ7ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በተላለፈው ውሳኔ መሠረት የተወሰነው ካፒታል ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ የተጠናቀቀ በመሆኑ አሁን ላይ የማህበሩ ካፒታል ማሳደግ የሚቻል መሆኑ ተጠቅሶ የማህበሩን ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ማሳደግ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው በተለይም የማህበሩን ገጽታ ከመገንባት አንጻር ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ተመላክቶ አሁን ያለውን ብር 30,324,000 (ሰላሳ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ አራት ሺህ ብር) የማህበሩ የተከፈለ ካፒታል አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት ወደ ብር 100,000,000 (አንድ መቶ ሚሊዮን ብር) እንዲያድግ ሀሳብ ቀርቦ ጉባዔው ተወያይቶበታል፡፡ አዳዲስ አክሲዮኖች ለነባር ባለአክሲዮኖች በያዙት አክሲዮን መጠን ተደልድሎ በቅድሚያ እንዲቀርቡ ስምምነት ተደርሷል፡፡ይህ ውሳኔም በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆንና ውሳኔውንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አስፈላጊ ተግባራት እንዲፈጽም ለማህበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣን መስጠቱ አስፈላጊ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

6.2.2 ውሳኔ፤

የፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ ጠቅላላ ጉባዔ ዛሬ ሕዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት ለነባር ባለአክሲዮኖች በያዙት አክሲዮን መጠን ተደልድሎ በቅድሚያ እንዲቀርቡ በማድረግ ብር 30,324,000 (ሰላሳ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ አራት ሺህ ብር) የሆነው የአክሲዮን ማህበሩን የተከፈለ ካፒታል (ዋና ገንዘብ) ወደ ብር 100,000,000 (አንድ መቶ ሚሊዮን ብር) እንዲያድግ ጉባዔው ላይ በተገኙት ባለአክሲዮኖች ሙሉ ድምጽ ተወስኗል፡፡ በተጨማሪም ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አስፈላጊ ተግባራት እንዲፈጽም የማህበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣን እንዲኖረውና ውሳኔው በአምስት አመታት ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ጉባዔው ላይ በተገኙት ባለአክሲዮኖች ሙሉ ድምጽ ተወስኗል፡፡

6.3 አጀንዳ 5.3 የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔ ማጽደቅ

6.3.1 የውይይቱ አጭር ቃል

በህዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም 9ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው የተነጋገረበት ቃለ ጉባዔ በዝርዝር ተመዝግቦ በጉባዔው ፊት በማህበሩው ፀሀፊ ተነብቦ ጉባዔው በሚገባ አዳምጧል፡፡

6.3.2 ውሣኔ

ጠቅላላ ጉባዔው ቃለ ጉባዔውን መርምሮ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

7. ለጉባኤው የቀረበ ሰነድ፣ የለም

8. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የማህበሩ ፀሀፊ ማረጋገጫ

እኛ የፒስ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማኀበር ዳይሬክተሮች እና የማሕበሩ ፀሐፊ ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) /ሰንጠረዥ 1/ ላይ ስማቸው፣ የፈረሙት እና የከፈሉት አክሲዮኖች ብዛት በስማቸው አንፃር በተመለከቱት ትይዩ የፈረሙ ባለአክሲዮኖች ሕዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ 9ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መገኘታቸውን ራሳቸው ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ላይ የተገለፁትን ውሣኔ ማሣለፋቸውን በሙሉ ስምና ፊርማችን እያረጋገጥን፣ በሰነዶቹ ላይ ስለተገለፁት ጉዳዮች እና ስለተላለፉት ውሣኔዎች ትክክለኛነት ስማቸው በሰነዶቹ ላይ በተዘረዘሩት ሰዎችም ሆነ በሌላ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወገን ለሚነሳ ማናቸውም የመጣ ተጠያቂ ኃላፊዎች መሆናችንን ጭምር እናረጋግጣለን፡፡

| ተ/ቁ | ሥም | ኃላፊነት | ፊርማ |
| --- | --- | --- | --- |
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የቦርድ ሰብሳቢ | |
| 2 | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | የቦርድ አባል | |
| 3 | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | የቦርድ አባል | |
| 4 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | የቦርድ አባል | |
| 5 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | የቦርድ አባል | |
| 6 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ (ተወካይ ወ/ሮ ዓይናለም አሸብር ገ/ህይወት) | የቦርድ አባል | |
| 7 | ወ/ሮ አዜብ በቀለ | የማህበሩ ፀሐፊ | |

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 53

...ments Authentication & ...Service Branch 10 Office

## የፒስ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር
## የባለአክሲዮኖች 9ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ
## የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance sheet) /ሰንጠረዥ 1/

| ተ.ቁ. | ስም ከነአያት | አድራሻ | የአክሲዮኖች ብዛት | | | | | የባለአክሲዮኑ ወይም የወኪሉ ስምና ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የአንዱ አክሲዮን ዋጋ | የተፈረመ | የተከፈለ | ያልተከፈለ | የድምጽ ቁጥር | |
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | አ.አ. ቦሌ ክ/ከ ቀ. 02 የቤት ቁ. 893 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | የለም | 2,500 | |
| 2 | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | አ.አ.ጉለሌ ክ/ከ ቀ. 19 የቤ.ቁ. 703 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 3 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | አ.አ. ቦሌክ/ከ የቤ.ቁ. 711 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | ያልተገኙ |
| 4 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | አ.አ. የካ ክ/ከ ቀ. 03 የቤ.ቁ. 1843 | 1,000.00 | 2,452 | 2,452 | “ | 2,452 | |
| 5 | ወ/ሮ ፀሀይ ፀጋዬ መከተ | አ.አ. የካ ክ/ከ ቀ. 13/14 የቤ.ቁ. 092 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 6 | ወ/ሮ ለበሰች ጸጋ ባለህ | አ.አ. የካ ክ/ከ ቀ. 13/14 የቤ.ቁ. 100 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 7 | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ ወ/ጊዮርጊስ | አ.አ. ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ቀ.12/13 የቤ.ቁ 415 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 8 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | አ.አ. የካ ክ/ከ ቀ. 08/15 የቤ.ቁ. 350 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 9 | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | አ.አ. ልፌ ቀራንዮክ/ከ ቀ. 15/16 የቤ.ቁ.38/137 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 10 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | አ.አ. ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ቀ. 15 የቤ.ቁ. 1287 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 11 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | አ.አ. ቂርቆስ ክ/ከ ቀ. 03 የቤ.ቁ. 379 | 1,000.00 | 129 | 129 | “ | 129 | |
| 12 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ሰሚነው | አ.አ. ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ.ከ ቀ 04 የቤ.ቁ. 1191 | 1,000.00 | 81 | 81 | “ | 81 | |
| 13 | ሲ/ር መሠረት ሺፈራው ይብራሁ | አ.አ. ቦሌ ክ/ከ ቀ. 19/19/20 የቤ.ቁ. 616 | 1,000.00 | 81 | 81 | “ | 81 | ያልተገኙ |
| 14 | ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ ተጫኔ | አ.አ. አራዳ ክ/ከ 2 ቀ.10 የቤ.ቁ. 184 | 1,000.00 | 81 | 81 | “ | 81 | ያልተገኙ |
| 15 | ወ/ት ፍላጐት ለማ ክብረት | አ.አ. አዲስ ከተማ ክ/ከ ቀ. 19/20 የቤ.ቁ. 099 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | | 2,500 | |
| 16 | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | ሻሸመኔ ወ. 2 ቀ. 05 የቤ.ቁ. 411 | 1,000.00 | 2,500 | 2,500 | | 2,500 | |
| ድምር | | | | 30,324 | 30,324 | | 30,324 | |

እኔ የፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ. የማህበሩ ፀሐፊ ይህ የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance sheet) በጉባኤው በአካል የተገኙ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎች የፈረሙበት ስለመሆኑ በሙሉ ሥም እና በፊርማዬ በንግድ ህግ አንቀጽ 378 (2) መሰረት አረጋግጣለሁ፡፡

የማህበሩ ፀሐፊ ሥም ________________

ፊርማ ________________